EUROPEAN UNION AGENCY FOR ASYLUM

# የቤተሰብ ማፈላለጊያ (አዋቂ)

# ቅፅ

ይህ ሰነድ በ2025 ነው የተጠናቀቀው
በዚህ ህትመት ላይ ካለ መረጃ ሊገኝ ስለሚችል ጥቅም የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅትም (EUAA) ሆነ ማንኛውም
በEUAA ስም የሚሰራ ማንኛውም ሰው ኃላፊነት አይወስድም።
ሉክዘምበርግ፦ የአውሮፓ ህብረት ህትመቶች ጽ/ቤት፣ 2025

PDF ISBN 978-92-9410-790-9 doi:10.2847/9517251 BZ-01-25-034-EN-N

© የአውሮፓ ህብረት የጥገኝነት ድርጅት (European Union Agency for Asylum)፣ 2025
ለምንጩ እውቅና እስከተሰጠ ድረስ፣ መልሶ ማተም/ማባዛት ይፈቀዳል።

| | |
|---|---|
| **የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ስም** | |
| **የብሔራዊ ባለሥልጣኑ አድራሻ** | |
| **ይህንን ቅጽ እንዴት እና የት እንደሚያስገቡ የሚገልጽ የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት-ተኮር መረጃ** | *ይህ የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራትቅጹን ስለሚያስገቡበት ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ የሚያስፍሩበት ቦታ ነው።*<br>*ይህ ቅጽ እንዴት መግባት አለበት? ወደ የትኛው አድራሻ? እስከ መቼ?* |

# የቤተሰብ ማፈላለግ ቅጽ (አዋቂ)

## ይህ ቅጽ ለምን ተሰጠኝ?

የዚህች ሀገር ባለስልጣናት ይህንን ቅጽ ([1]) የሰጡዎት ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ጥያቄ ስላቀረቡ እና በአውሮፓ ህብረት አባል ሀገር ወይም በተዛማጅ ሀገር (የአውሮፓ ህብረት+ ሀገሮች በመባል የሚታወቁ) የቤተሰብ አባል እንዳለዎት ተናግረዋል።

| |
|---|
| የአውሮፓ ሕብረት አባል ሀገራት ቤልጂየም፣ ቡልጋሪያ፣ ቼክያ፣ ዴንማርክ፣ ጀርመን፣ ኢስቶኒያ፣ አይርላንድ፣ ግሪክ፣ ስፔን፣ ፈረንሳይ፣ ክሮኤሺያ፣ ጣሊያን፣ ሳይፕረስ፣ ላቲቪያ፣ ሊቱዌኒያ፣ ሉክሰምበርግ፣ ሃንጋሪ፣ ማልታ፣ ኔዘርላንድስ፣ ኦስትሪያ፣ ፖላንድ፣ ፖርቱጋል፣ ሮማኒያ፣ ስሎቬኒያ፣ ስሎቫኪያ፣ ፊንላንድ እና ስዊድን ናቸው። አራቱ ተባባሪ ሀገራት አይስላንድ፣ ሊችተንስታይን፣ ኖርዌይ እና ስዊዘርላንድ ናቸው። |

በዚህ ቅጽ ላይ የሚሰጡት መረጃ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት የቤተሰብ አባላትዎን እንዲያገኙ፣ ለጉዳይዎ ቅድሚያ እንዲሰጡ እና ማመልከቻዎን ሊመረምር የሚገባውን የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር እንዲለዩ ይረዳቸዋል። በሌላ የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ የቤተሰብ አባላት ስላሉዎት፣ የቤተሰብ አባልዎ ያለበት ሀገር የእርስዎን ማመልከቻ የመመርመር ኃላፊነት ሊኖርበት ይችላል።

**አስፈላጊ።** ይህንን ቅጽ ለመሙላት ማንኛውም ዓይነት ድጋፍ የሚያስፈልግዎ ከሆነ ለባለሥልጣናቱ ያሳውቁ።

## ይህንን ቅጽ እንድሞላ ለምን ተጠየቅኩ?

በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት በማንኛውም የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት ውስጥ የቤተሰብ አባላት ካሉዎት ማወቅ ይፈልጋሉ። ካሉዎት፣ እነሱ የሚኖሩበት ሀገር የእርስዎን ማመልከቻ የማስተናገድ ኃላፊነት ሊኖርበት ይችላል።

በተጨማሪም በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት፣ ከእነሱ ጋር መሆን ከፈለጉ፣ በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት ካሉ የቤተሰብዎ አባላት ጋር እንዲገናኙ ሊረዱዎት ይፈልጋሉ። ከቤተሰብዎ አባል ጋር መገናኘት ከፈለጉ ያሳውቁን፤ እኛም ይህ ሊሆን የሚችልበትን መንገድ እንመረምራለን፣ እንዲሳካም እንጥራለን። መገናኘት የማይፈልጉ ከሆነ በተቻለ ፍጥነት ይንገሩን።

### ከማን ጋር ነው መገናኘት የምችለው?

ቀድሞውኑ በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ ከሚኖር የቤተሰብ አባል ጋር መገናኘት ይችላሉ። እነዚህም፡-

- ሚስትዎ ወይም ባልዎ - ይህ ሰው የትዳር አጋር ይባላል፤

([1]) PDF:- BZ-01-25-006-EN-N and Print BZ-01-25-006-EN-C.

- ያልተጋቡ ነገር ግን የተረጋጋ የፍቅር ግንኙነት ያለዎት አጋርዎ ([2])፤
- ከ18 ዓመት በታች የሆነ ልጅዎ ([3])።

እንዲሁም የእርስዎን እንክብካቤ የሚፈልግን ሰው ወይም በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ በእርሱ እንክብካቤ ላይ ጥገኛ የሆኑበትን ሰው ማግኘት ይችላሉ፡-

- እርግዝና፣
- አዲስ የተወለደ ልጅ መኖር፣
- ከባድ የአእምሮ ሕመም፤
- ከባድ የአካል ሕመም፤
- ከባድ የአካል ጉዳት፣
- ከባድ የስነ ልቦና ጉዳት፣
- እርጅና።

ይህ ሰው የሚከተሉት ሊሆን ይችላል፡-

- ልጅዎ (ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወይም አዋቂ)፤
- ወንድምዎ ወይም እህትዎ፤
- ወላጅዎ።

## በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ የቤተሰብ አባል ካለዎት የሚከተሉት መብቶች አሉዎት።

- በዚህ ቅጽ አሞላል ላይ ድጋፍ ሊሰጡዎት ከሚችሉ ግለሰቦች እና ተቋማት መረጃ የመጠየቅ መብት አለዎት።
- የቤተሰብ አባላትዎን ለመለየት እና ለመፈለግ ሊረዱ ስለሚችሉ ብሔራዊ፣ ዓለም አቀፍ እና ሌሎች ተዛማጅ ድርጅቶች መረጃ የመጠየቅ መብት አለዎት።
- የቃለ መጠይቅ አስፈላጊነትን የሚያስቀሩ ምክንያቶች ከሌሉ በስተቀር፣ የእርስዎን የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ የመመርመር ኃላፊነት ያለበትን የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ለመወሰን ቃለ መጠይቅ ሊደረግልዎት ይችላል።
- የቤተሰብ አባላት መኖራቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ ማንኛውንም መረጃ በቃል ወይም በሰነድ ማቅረብ ይችላሉ።
- ስለ ጉዳይዎ ተጨማሪ መረጃ የመጠየቅ መብት አለዎት።

## በዚህ ቅጽ ውስጥ ምን ማካተት ይኖርብኛል?

**በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት ከቤተሰብ አባላትዎ ጋር እንዲያገናኙዎት ለመርዳት፣ ስለ እነርሱ የቻሉትን ያህል ብዙ መረጃ ሊያካፍሉን ይገባል።** ይህም በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ ስለሚገኝ የቤተሰብ አባልዎ ወይም የእንክብካቤ ጥገኝነት ስላላችሁ ሰው የሚከተሉትን መሠረታዊ መረጃዎች ማካተትን ያካትታል፡-

- የግል ዝርዝር መረጃዎቻቸው፤
- በአሁኑ ወቅት የሚኖሩበት ቦታ፤
- የመገናኛ አድራሻዎቻቸው፤
- በዚያ ሀገር ስላላቸው ሕጋዊ ሁኔታ የሚገልጽ መረጃ (የጥገኝነት ጠያቂነት ሁኔታ ወይም የስደተኛ ወረቀት፣ የነዋሪነት ፈቃድ ካላቸው፣ ወይም በቀድሞ ዓለም አቀፍ ጥበቃ ሁኔታ ላይ ተመስርተው የዚያ ሀገር ዜጋ ከሆኑ)፤
- ዝምድናዎን የሚያረጋግጡ ማናቸውም ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች።

([2]) የአውሮፓ ሕብረት+ አገሩ ሕግ ወይም አሠራር፣ ጋብቻ ያልመሠረቱ ጥንዶችን ከውጭ ሀገር ዜጎች ጋር በተያያዘ ከባለትዳሮች ጋር እኩል የሚመለከታቸው ከሆነ።
([3]) ይህ የሚያመለክተው የወለዱትን ወይም በሕግ የጉዲፈቻ ልጅ አድርገው የተቀበሉትን ልጅ ነው።

## ይህ መረጃ ለምን አስፈላጊ ሆነ?

የሚሰጡት መረጃ በጨመረ ቁጥር፣ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት የቤተሰብ አባልዎ ባለበት ሀገር ካሉ ባለሥልጣናት ጋር ለመገናኘት፣ ዝምድናዎን ለማረጋገጥ እና በተቻለ ፍጥነት እናንተን ለማገናኘት ቀላል ይሆንላቸዋል።

ስለ ዝምድናው እና ግለሰቡ ስለሚገኝበት ቦታ የበለጠ ለማወቅ ለቃለ መጠይቅ ሊጠሩ ወይም ተጨማሪ ጥያቄዎች ሊጠየቁ ይችላሉ።

ሁሉንም መረጃ ባይኖርዎትም አይጨነቁ። የቻሉትን ያህል ይሙሉ፤ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት ሂደቱን ለመጀመር የተቻላቸውን ጥረት ያደርጋሉ። ማናቸውም ሰነዶች ካሉዎት፣ በተቻለ ፍጥነት በዚህ ሀገር ለሚገኙ ባለሥልጣናት ያስገቡ።

## ይህንን ቅጽ እንዴት መሙላት ይቻላል?

**ደረጃ 1።** የቅጹን ክፍል 1 ይሙሉ። ይህ የእርስዎን የግል መረጃ የሚሰበስብ ክፍል ነው።

**ደረጃ 2።** ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚመለከተውን የቅጹን ክፍል ይሙሉ፡-

- የትዳር አጋር ወይም ያልተጋቡ የፍቅር አጋር (ክፍል 2)
- ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ (ክፍል 3)፡-
  *በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት ውስጥ ከአንድ በላይ ልጆች ካሉዎት፣ ለእያንዳንዱ ልጅ ይህንን የቅጹን ክፍል ለየብቻ ይሙሉ።*
- ጥገኛ ሰው (ክፍል 4)፡-
  *ይህንን ክፍል የሚሞሉት የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲኖሩ ነው፡-*
  - የእርስዎ (አዋቂ) ልጅ፣ ወንድም/እህት ወይም ወላጅ በተጋላጭ ሁኔታ ላይ በመሆናቸው የእርስዎን እንክብካቤ የሚፈልጉ ከሆነ፤
  - እርስዎ በተጋላጭ ሁኔታ ላይ ሆነው በ(አዋቂ) ልጅዎ፣ በወንድም/እህትዎ ወይም በወላጅዎ እንክብካቤ ላይ ጥገኛ ከሆኑ።

**ደረጃ 3።** ሁሉንም የቤተሰብ አባላት ለማመልከት የቤተሰብ ሐረግዎን ይሳሉ (ክፍል 5)። ይህ ለወደፊት የቤተሰብ ፍለጋ ጥረቶች ወይም ዳግም መገናኘት ሲጀመርባቸው የሚችሉ ሌሎች ሰዎች መኖራቸውን ለመረዳት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

## ቅጹን ለመሙላት ማን ሊረዳኝ ይችላል?

ይህንን ቅጽ ለመሙላት የሕግ ድጋፍን ጨምሮ ማንኛውም እርዳታ ካስፈለገዎት መጠየቅ ይችላሉ። ያልተረዳችሁት ነገር ካለ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናትን እርዳታ መጠየቅ ትችላላችሁ። ስለ ሕግ አማካሪዎች ስብስብ ተጨማሪ መረጃ የኃላፊነት ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን በሚመለከት በሚሰጠው የመረጃ በራሪ ጽሑፍ ላይ ማግኘት ይችላሉ። ቅጹን ለመሙላት የቋንቋ እገዛንም መጠየቅ ይችላሉ።

*ቅጹን በመሙላት ረገድ እገዛ እና የሕግ አማካሪነት ስለሚሰጡ ግለሰቦች እና ተቋማት የሚገልጽ ለእያንዳንዱ የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር የተለየ መረጃ።*

## ከቤተሰብ አባሌ ጋር እንዴት ዳግም መገናኘት እችላለሁ?

- በመጀመሪያ፣ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት የሰጡትን መረጃ ይገመግማሉ። ለሌላ ቃለ መጠይቅም ሊጠሩዎት ይችላሉ።
- ቢቻል፣ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት የቤተሰብ አባልዎ ወደሚኖርበት የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ጥያቄ ይልካሉ።

**አስፈላጊ**። ለዳግም መገናኘቱ እርስዎም ሆኑ የቤተሰብ አባልዎ መስማማት አለባችሁ። ከእናንተ መካከል አንዱ "አልስማማም" ካለ፣ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት ሂደቱን አይቀጥሉም። ከተስማሙ፣ ለዳግም መገናኘቱ መደበኛ የጽሑፍ ስምምነትዎን እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። ስምምነትዎን በተለየ ቅጽ ላይ ማቅረብ ይኖርብዎታል።

- የቤተሰብ አባልዎ የሚኖርበት ሀገር የቀረበውን ጥያቄ ይገመግማል፣ ሰነዶቹንም ያጣራል።
- ጥያቄውን ከተቀበሉት፣ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት ከቤተሰብዎ ጋር እንዲገናኙ ወደዚያ ሀገር ያስተላልፋዎታል።

በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት ያለ ፍላጎትዎ ከማንም ሰው ጋር አያገናኙዎትም። ስምምነት ማለት የእርስዎ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ የቤተሰብ አባልዎ ወይም ጥገኛ የሆነው ሰው በሚኖርበት ሀገር እንዲመረመር ሁለታችሁም መስማማታችሁን ያሳያል። እርስዎ ወይም የቤተሰብ አባልዎ ካልተስማማችሁ፣ በዚህ ሀገር ያሉ ባለሥልጣናት የዳግም መገናኘት ሂደቱን አይጀምሩም። የማስተላለፍ ወይም ዝውውር ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ስምምነትዎን ማንሳት (መሰረዝ) ይችላሉ።

በሁለቱም ሀገራት፣ የቤተሰብ ዳግም መገናኘት ጉዳዮች ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። ይህም ማለት በእርስዎ ጉዳይ ላይ የቤተሰብ ዳግም መገናኘት ሊጀመር የሚችል ከሆነ፣ ባለሥልጣናቱ በተቻለ ፍጥነት ሂደቱን ያከናውናሉ ማለት ነው።

### ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

- የመዘዋወር ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ሃሳብዎን የመቀየር እና ስምምነትዎን የመሰረዝ መብት አለዎት።
- ከቤተሰብዎ ጋር ዳግም ለመገናኘት ለማንም ሰው መክፈል አያስፈልግዎትም – ወጪውን ባለሥልጣናቱ ይሸፍኑታል።
- የቤተሰብ ዳግም መገናኘት ጉዳዮች ቅድሚያ የሚሰጣቸው በመሆኑ፣ ባለሥልጣናቱ ጉዳይዎን በተቻለ ፍጥነት ያከናውናሉ።

### ዳግም መገናኘት (Reunification) ምን ማለት ነው?

- የእርስዎ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ የቤተሰብ አባልዎ በሕጋዊ መንገድ በሚኖርበት ሀገር ይመረመራል (4)።

ዳግም መገናኘት ማለት በዚያ ሀገር ውስጥ የነዋሪነት ፈቃድ ወዲያውኑ ያገኛሉ ማለት አይደለም።

## የቤተሰብ አባሌ ያለበትን ቦታ አላውቅም። ልትረዱኝ ትችላላቹ?

የቤተሰብዎ አባል በአንድ የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ መኖሩን ካወቁ ነገር ግን በትክክል የት እንዳሉ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ የቤተሰብ አባልዎን ለማግኘት ሊረዱዎት የሚችሉ የቤተሰብ ፍለጋ ድርጅቶችን እገዛ መጠየቅ ይችላሉ። እንዲህ ዓይነት ድጋፍ የሚያስፈልግዎ ከሆነ በዚህ ሀገር ላሉ ባለሥልጣናት ያሳውቁ።

(4) በሕጋዊ መንገድ መኖር ማለት በአንድ ሀገር ውስጥ ለመግባት፣ ለመቆየት ወይም ለመኖር የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያሟላሉ ማለት ነው።

*ስለ ቤተሰብ ፍለጋ ድርጅቶች የሚገልጽ ለእያንዳንዱ የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር የተለየ መረጃ።*

## የምሰጠው መረጃ እንዴት ነው የሚያዘው (ጥበቃ የሚደረግለት)?

የሚሰጡት መረጃ በሚስጥር ይያዛል። መረጃው በዚህ ቅጽ ገጽ 1 ላይ ከተጠቀሱት የአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት ውጭ ላለ ማንኛውም ሀገር፣ ወይም ለእርስዎም ሆነ ለቤተሰብዎ የትውልድ ሀገር ወይም ቀደም ሲል በቋሚነት ለኖሩበት ሀገር በፍጹም ተላልፎ አይሰጥም። የዚያ ሀገር ባለሥልጣናት የእርስዎ ዝምድና ለቤተሰብ ዳግም መገናኘት ብቁ መሆኑን መወሰን እንዲችሉ፣ መረጃው የቤተሰብ አባልዎ ላለበት የአውሮፓ ሕብረት+ሀገር ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ይላካል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ባለሥልጣናት ወይም ድርጅቶች ለተጨማሪ ጥያቄዎች የቤተሰብ አባልዎን ሊያነጋግሩ ይችላሉ።

| ክፍል 1። የአመልካቹ የግል መረጃ | |
|---|---|
| **የመዝገብ ቁጥር፡-** | |
| የመጀመሪያ ስም | |
| የአያት ስም/የቤተሰብ ስም | |
| ዕድሜ | |
| ፆታ | |
| የትውልድ ቀን (ቀን/ወር/ዓመት) | |
| የትውልድ ቦታ | |
| ከመነሻ ሀገር የወጡበት ቀን | |
| ዜግነት/ዜግነቶች | |
| አድራሻ/መኖሪያ ቦታ | |
| የመገናኛ ዘዴዎች (የኢሜይል አድራሻ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ አካውንት፣ ስልክ ቁጥር) | |
| ☐ **በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ የሚኖር የቤተሰብ አባል እንዳለኝ አረጋግጣለሁ።** | |
| የእኔ የቤተሰብ አባል (ከአንድ በላይ መምረጥ ይቻላል) | ☐ የእኔ የትዳር አጋር ወይም ያላገባሁት/ያላገባኋት የፍቅር አጋር (ክፍል 2)<br>☐ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ (ክፍል 3)<br>☐ በእኔ እንክብካቤ ላይ ያለ ወይም እኔ በእርሱ እንክብካቤ ላይ ጥገኛ የሆንኩበት ሰው (ክፍል 4) |
| ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች | |
| **የአመልካቹ ፊርማ እና ቀን** | |

| ክፍል 2፡፡ የትዳር አጋር ወይም ያልተጋቡ የፍቅር አጋር የግል መረጃ | |
|---|---|
| የመጀመሪያ ስም | |
| የአያት ስም/የቤተሰብ ስም | |
| ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ስሞች | |
| ዕድሜ | |
| ፆታ | |
| የትውልድ ቀን (ቀን/ወር/ዓመት) | |
| የትውልድ ቦታ | |
| ጋብቻ የተፈጸመበት ወይም ግንኙነቱ የተመሠረተበት ቦታ | |
| የጋብቻ ቀን ወይም ግንኙነቱ የተጀመረበት ቀን | |
| የጋብቻ ወይም የጥምረት ዓይነት (ከአንድ በላይ መምረጥ ይቻላል) | ☐ ሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓት<br>☐ የሲቪል ምዝገባ (መንግስታዊ)<br>☐ የተመዘገበ የሲቪል ጥምረት<br>☐ ሌላ (እባክዎን ይጥቀሱ)፡- |
| በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት ውስጥ በአሁኑ ወቅት የሚገኙበት ወይም ለመጨረሻ ጊዜ የሚታወቁበት ቦታ (ሀገር፣ ከተማ) | |
| ግለሰቡ በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ ያለው የነዋሪነት ሁኔታ | ☐ የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች<br>☐ የአለም አቀፍ ጥበቃ ተጠቃሚ<br>☐ የረጅም ጊዜ ነዋሪነት<br>☐ ነዋሪ<br>☐ ዜጋ<br>☐ አይታወቅም |
| ከመነሻ ሀገር የወጡበት ቀን | |
| ዜግነት/ዜግነቶች | |
| የግል መታወቂያ ቁጥር / የመዝገብ ቁጥር (በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ የሚገኝ የመለያ ቁጥር ካለ) | |
| አድራሻ/መኖሪያ ቦታ | |
| የመገናኛ ዘዴዎች (የኢሜይል አድራሻ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ አካውንት፣ ስልክ ቁጥር) | |

**ዳግም ለመገናኘት ያለው ፍላጎት**

ከዚህ ሰው ጋር ዳግም መገናኘት ይፈልጋሉ?

☐ አዎ፣ ዳግም መገናኘት እፈልጋለሁ።

**በዚህ ሁኔታ፣ እርስዎ እና የቤተሰብ አባልዎ መደበኛ የጽሑፍ ስምምነት እንድትሰጡ ትጠየቃላችሁ። መደበኛው ስምምነት በሌላ ቅጽ ላይ እንዲሰጥ ይጠየቃል።**

☐ አይ፣ ዳግም መገናኘት አልፈልግም።

ዳግም መገናኘት የማይፈልጉ ከሆነ፣ ምክንያቱን ማብራራት ይችላሉ። ይህ መረጃ በሚስጥር ይያዛል።

| |
|---|
| **ስለ ተጋላጭነት ሁኔታዎች ወይም ሰብአዊ ምክንያቶች የሚገልጽ ተዛማጅ መረጃ** |
| ስለ ቤተሰብዎ አባል ባለሥልጣናት ሊያውቁት የሚገባ ማንኛውንም ተዛማጅ መረጃ እዚህ መጥቀስ ይችላሉ (ማንኛውም ተጋላጭነት፣ ልዩ ፍላጎቶች ወይም ሰብአዊ ምክንያቶች) |
| **ከዚህ ሰው ጋር ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኙት መቼ እና የት ነበር?** |
| |
| **የቤተሰብ አባልዎ ያለበትን ቦታ ሊያውቅ የሚችል ሌላ ሰው አለ? ካለ፣ እባክዎን የመገናኛ አድራሻቸውን ይስጡ። ይህንን ሰው አግኝተውታል?** |
| |
| ***ይህንን ሰው ለመፈለግ ማንኛውንም ድርጅት አነጋግረዋል? አዎ ከሆነ፣ እባክዎን በዝርዝር ያብራሩ (የድርጅቱ ስም፣ የፍለጋው ደረጃ / ውጤት)።*** |
| |
| **ዝምድናውን የሚያረጋግጡ ያሉዎትን ሰነዶች/ማስረጃዎች ይግለጹ።**<br>ለምሳሌ የጋብቻ ምስክር ወረቀት፣ የልደት ምስክር ወረቀት፣ የመታወቂያ ሰነዶች ቅጂ፣ የቤተሰብ አባል ፎቶግራፎች፣ ወይም ሌሎች። እነዚህን ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። |
| |
| **ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች** |
| |

| ክፍል 3፡ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ የግል መረጃ | |
|---|---|
| *በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት ውስጥ ከአንድ በላይ ልጆች ካሉዎት፣ ለእያንዳንዱ ልጅ አዲስ ክፍል ለመፍጠር 'ክፍሉን አባዛ' (Duplicate section) የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።* | |
| የመጀመሪያ ስም | |
| የአያት ስም/የቤተሰብ ስም | |
| ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ስሞች | |
| ዕድሜ | |
| ፆታ | |
| የትውልድ ቀን (ቀን/ወር/ዓመት) | |
| የትውልድ ቦታ | |
| በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት ውስጥ በአሁኑ ወቅት የሚገኙበት ወይም ለመጨረሻ ጊዜ የሚታወቁበት ቦታ (ሀገር፣ ከተማ) | |
| ግለሰቡ በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ ያለው የነዋሪነት ሁኔታ | ☐ የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች<br>☐ የአለም አቀፍ ጥበቃ ተጠቃሚ<br>☐ የረጅም ጊዜ ነዋሪነት<br>☐ ነዋሪ<br>☐ ዜጋ<br>☐ አይታወቅም |
| ከመነሻ ሀገር የወጡበት ቀን | |
| ዜግነት/ዜግነቶች | |
| የግል መታወቂያ ቁጥር / የመዝገብ ቁጥር (በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ የሚገኝ የመለያ ቁጥር ካለ) | |
| አድራሻ/መኖሪያ ቦታ | |
| የመገናኛ ዘዴዎች (የኢሜይል አድራሻ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ አካውንት፣ ስልክ ቁጥር) | |
| **ካለ፣ የአሳዳጊው የመገናኛ አድራሻ** | |
| የመጀመሪያ ስም | |
| የአያት ስም/የቤተሰብ ስም | |
| የስልክ ቁጥር | |
| የኢሜይል አድራሻ | |
| **ዳግም ለመገናኘት ያለው ፍላጎት** | |
| ከዚህ ሰው ጋር ዳግም መገናኘት ይፈልጋሉ?<br>☐ አዎ፣ ዳግም መገናኘት እፈልጋለሁ።<br>**በዚህ ሁኔታ፣ እርስዎ እና የቤተሰብ አባልዎ መደበኛ የጽሑፍ ስምምነት እንድትሰጡ ትጠየቃላችሁ። መደበኛው ስምምነት በሌላ ቅጽ ላይ እንዲሰጥ ይጠየቃል።**<br>☐ አይ፣ ዳግም መገናኘት አልፈልግም።<br>ዳግም መገናኘት የማይፈልጉ ከሆነ፣ ምክንያቱን ማብራራት ይችላሉ። ይህ መረጃ በሚስጥር ይያዛል። | |

| |
|---|
| **ስለ ተጋላጭነት ሁኔታዎች ወይም ሰብአዊ ምክንያቶች የሚገልጽ ተዛማጅ መረጃ** |
| ስለ ቤተሰብዎ አባል ባለሥልጣናት ሊያውቁት የሚገባ ማንኛውንም ተዛማጅ መረጃ እዚህ መጥቀስ ይችላሉ (ማንኛውም ተጋላጭነት፣ ልዩ ፍላጎቶች ወይም ሰብአዊ ምክንያቶች) |
| **ከዚህ ሰው ጋር ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኙት መቼ እና የት ነበር?** |
| |
| **የቤተሰብ አባልዎ ያለበትን ቦታ ሊያውቅ የሚችል ሌላ ሰው አለ? ካለ፣ እባክዎን የመገናኛ አድራሻቸውን ይስጡ። ይህንን ሰው አግኝተውታል?** |
| |
| **ይህንን ሰው ለመፈለግ ማንኛውንም ድርጅት አነጋግረዋል? አዎ ከሆነ፣ እባክዎን በዝርዝር ያብራሩ (የድርጅቱ ስም፣ የፍለጋው ደረጃ / ውጤት)።** |
| |
| **ዝምድናውን የሚያረጋግጡ ያሉዎትን ሰነዶች/ማስረጃዎች ይግለጹ።** ለምሳሌ የጋብቻ ምስክር ወረቀት፣ የልደት ምስክር ወረቀት፣ የመታወቂያ ሰነዶች ቅጂ፣ የቤተሰብ አባል ፎቶግራፎች፣ ወይም ሌሎች። እነዚህን ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። |
| |
| **ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች** |
| |


| ክፍል 4፡ ከጥገኛ ሰው ጋር የተያያዘ የግል መረጃ | |
|---|---|
| *እርስዎ በእነሱ ላይ ጥገኛ የሆኑባቸው ወይም በእርስዎ ላይ ጥገኛ የሆኑ ከአንድ በላይ ልጆች፣ ወንድሞች/እህቶች ወይም ወላጆች ካሉዎት፣ ለእያንዳንዱ ግለሰብ አዲስ ክፍል ለመፍጠር 'ክፍሉን አባዛ' (Duplicate section')የሚለውን ቁልፍ ይጫኑ።* | |
| ከግለሰቡ ጋር ያለዎት ዝምድና፡- | ☐ ልጅ (አዋቂ)<br>☐ ወንድም ወይም እህት<br>☐ ወላጅ |
| **እባክዎን ይምረጡ፡-**<br>☐ ይህ ሰው በእኔ እርዳታ/እንክብካቤ ላይ ጥገኛ ነው።<br>☐ እኔ በዚህ ሰው እርዳታ/እንክብካቤ ላይ ጥገኛ ነኝ። | |
| የመጀመሪያ ስም | |
| የአያት ስም/የቤተሰብ ስም | |
| ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ስሞች | |
| ዕድሜ | |
| ፆታ | |
| የትውልድ ቀን (ቀን/ወር/ዓመት) | |
| የትውልድ ቦታ | |
| የጥገኝነት ትስስር ዓይነት (ከአንድ በላይ መምረጥ ይቻላል) | ይህ ሰው በእርስዎ እርዳታ ላይ ጥገኛ የሆነበትን ወይም እርስዎ በዚህ ሰው እርዳታ ላይ ጥገኛ የሆኑበትን ምክንያት ይምረጡ፡-<br>☐ እርግዝና<br>☐ አራስ ልጅን መንከባከብ<br>☐ በከባድ የአእምሮ ሕመም የሚሰቃይ<br>☐ በከባድ የአካል ሕመም የሚሰቃይ<br>☐ ከባድ የአካል ጉዳት<br>☐ ከባድ የስነ ልቦና ጉዳት<br>☐ እርጅና<br>☐ ሌላ (እባክዎን ይጥቀሱ)፡- |
| በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገራት ውስጥ በአሁኑ ወቅት የሚገኙበት ቦታ (ሀገር፣ ከተማ) | |
| ግለሰቡ በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ ያለው የነዋሪነት ሁኔታ | ☐ የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች<br>☐ የአለም አቀፍ ጥበቃ ተጠቃሚ<br>☐ የረጅም ጊዜ ነዋሪነት<br>☐ ነዋሪ<br>☐ ዜጋ<br>☐ አይታወቅም |
| ከመነሻ ሀገር የወጡበት ቀን | |
| ዜግነት/ዜግነቶች | |
| የግል መታወቂያ ቁጥር / የመዝገብ ቁጥር (በአውሮፓ ሕብረት+ ሀገር ውስጥ የሚገኝ የመለያ ቁጥር ካለ) | |
| አድራሻ/መኖሪያ ቦታ | |
| የመገናኛ ዘዴዎች (የኢሜይል አድራሻ፣ የማኅበራዊ ሚዲያ አካውንት፣ ስልክ ቁጥር) | |

| |
|---|
| **ዳግም ለመገናኘት ያለው ፍላጎት** |
| ከዚህ ሰው ጋር ዳግም መገናኘት ይፈልጋሉ?<br>☐ አዎ፣ ዳግም መገናኘት እፈልጋለሁ።<br>**በዚህ ሁኔታ፣ እርስዎ እና የቤተሰብ አባልዎ መደበኛ የጽሑፍ ስምምነት እንድትሰጡ ትጠየቃላችሁ። መደበኛው ስምምነት በሌላ ቅጽ ላይ እንዲሰጥ ይጠየቃል።**<br>☐ አይ፣ ዳግም መገናኘት አልፈልግም።<br>ዳግም መገናኘት የማይፈልጉ ከሆነ፣ ምክንያቱን ማብራራት ይችላሉ። ይህ መረጃ በሚስጥር ይያዛል። |
| **ስለ ተጋላጭነት ሁኔታዎች ወይም ሰብአዊ ምክንያቶች የሚገልጽ ተዛማጅ መረጃ** |
| ስለ ቤተሰብዎ አባል ባለሥልጣናት ሊያውቁት የሚገባ ማንኛውንም ተዛማጅ መረጃ እዚህ መጥቀስ ይችላሉ (ማንኛውም ተጋላጭነት፣ ልዩ ፍላጎቶች ወይም ሰብአዊ ምክንያቶች) |
| **ከዚህ ሰው ጋር ለመጨረሻ ጊዜ የተገናኙት መቼ እና የት ነበር?** |
| |
| **የቤተሰብ አባልዎ ያለበትን ቦታ ሊያውቅ የሚችል ሌላ ሰው አለ? ካለ፣ እባክዎን የመገናኛ አድራሻቸውን ይስጡ። ይህንን ሰው አግኝተውታል?** |
| |
| ***ይህንን ሰው ለመፈለግ ማንኛውንም ድርጅት አነጋግረዋል? አዎ ከሆነ፣ እባክዎን በዝርዝር ያብራሩ (የድርጅቱ ስም፣ የፍለጋው ደረጃ / ውጤት)።*** |
| |
| **ዝምድናውን የሚያረጋግጡ ያሉዎትን ሰነዶች/ማስረጃዎች ይግለጹ።**<br>ለምሳሌ የጋብቻ ምስክር ወረቀት፣ የልደት ምስክር ወረቀት፣ የመታወቂያ ሰነዶች ቅጂ፣ የቤተሰብ አባል ፎቶግራፎች፣ ወይም ሌሎች። እነዚህን ሰነዶች ወይም ማስረጃዎች እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። |
| |
| **ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች** |
| |

ክፍሉን አባዛ

## ክፍል 5። የቤተሰብ ሐረግ (አማራጭ)

ከታች ባለው ሳጥን ውስጥ የቤተሰብ ሐረግዎን መሳል ይችላሉ። የቅርብ የቤተሰብ አባላትዎን መጥቀስዎን ያረጋግጡ። የቅርብ የቤተሰብ አባላት የሚባሉት የትዳር አጋርዎ፣ ልጅ ወይም ልጆችዎ፣ ወላጆችዎ እና ወንድም/እህቶችዎ ናቸው። ቢቻል፣ የቤተሰብ አባልዎ በአሁኑ ወቅት በየትኛው ሀገር እንደሚኖር ያመልክቱ። የቤተሰብ ሐረግ ምሳሌ ከታች ባለው ምስል ላይ ይታያል።




*ከማንኛውም ተጨማሪ የቤተሰብ አባላት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በዚህ ክፍል ውስጥ ያስገቡ*